# በዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ የተጠበቁ ባህሪዎች

Office of Human Rights
DISTRICT OF COLUMBIA

የዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ የዲሲን የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌን በኮሎምብያ ዲስትሪክት ለሚኖሩ፣ለሚጎበኙ ወይም ለሚሠሩ ሰዎች በ19 ባህሪዎች ላይ የተመሠረቱ የአድሎ በህሪዎችን ህገወጥነት ያስከብራል። የዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ በቤት፣ በሥራ፣ በህዝብ መኖርያ ቤቶች እና የትምህርት ተቋማት የሚፈፀም አድሎን ይከለክላል።

ለቤት፣ ለሥራ፣ ለህዝብ መኖሪያዎች እና ለትምህርት ተቋማት የተጠበቁ ባህሪዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፣

1. ዘር፣ ግለሰብን በትውልድ ወይም በጎሳ መደልደል
2. ቀለም፣ የቆዳ ቀለም ወይም መልክ
3. ኃይማኖት፣ መንፈሳዊነትን የሚያካትት ወይም የማያካትት የእምነት ሥርዓት
4. የትውልድ ሀገር: የአንድ ሰው የትውልድ ሀረግ ከየትኛው አገር ወይም አካባቢ እንደሆነ
5. ፆታ፣ የሰውን ፆታ፣ የፆታ ውካቤን እና የሴትን የጡት ማጥባት መብትን ያካታትታል
6. ዕድሜ፣ 18 ዓመት ወይም በላይ
7. የጋብቻ ሁኔታ፣ ያገባ (አንድ ዓይነት ፆታ ወይም ተቃራኒ ፆታ)፣ ያላጋባ፣ የቤት ውስጥ ጓደኝነት፣ የተፋታ፣ የተለያዩ፣ እና በሞት የተለየ
8. የሰውነት ገጽታ፣ የውጭ አመለካከት፣ ሆኖም ከሥራ አስፈላጊነት ወይም መመዘኛ ጋር የተያያዘ
9. የፆታ አመለካከት: ተመሳሳይ ፆታ፣ ተቃራኒ ፆታ፣ እና ባለ ሁለት ፆታ
10. የፆታ መለያ ወይም አስተያየት፣ ከፆታ ጋር የተያያዘ መለያ፣ ጠባይ፣ ገጽታ፣ አመለካከት ወይም ሲወለዱ ከነበረዎት የተለየ ጠባይ
11. የቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ በልጆችዎ፣ በልጅ ልጆችዎ እና በወላጆችዎ ብቻ ያልተወሰነ በጥገኝነት ላይ ያለ ሰውን መርዳት
12. የፖለቲካ ግንኙነት፣ ለፖለቲካ ፓርቲ ያለዎት ድጋፍ ወይም ግንኙነት
13. የአካል ጉዳት፣ ከዋና የህይወት እንቅስቃሴዎች በአንዱ ወይም ከዛም በላይ በሰፊው እንዳይሳተፉ የሚወስንዎት የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት (ኤች አይቪ/ ኤድስን ጨምሮ)

በአንዳንድ ሁኔታ አግባብነት ያላቸው ተጨማሪ ጠባዮች የሚከተሉትን ያካትታሉ፣

14. ምዝገባ፣ (የቤት፣ የሥራ እና የሕዝብ መኖሪያዎችን ያካትታል)፣ ኮሌጅ፣ ዩኒቨርስቲ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መግባት
15. የቤተሰብ ሁኔታ (የቤት፣ የህዝብ መኖሪያዎችን እና የትምህርት ተቋማትን ያጠቃልላል)፣ ከ18 ዓመት በታች ልጅ ያላው ወላጅ ወይም አሳዳጊ
16. የዘር መረጃ (ሥራን እና የሕዝብ መኖሪያዎችን ያጠቃልላል)፣ የአንድ ሰውን በበሽታ መያዝን ወይም መታመምን ሊያመልከት የሚችል የ DNA ወይም የቤተሰብ ታሪክ
17. የገቢ ምንጭ (የቤት እና የትምህርት ተቋማትን ያካትታል)፣ የአንድ ሰው የገንዘብ ምንጩን
18. የመኖርያ ወይም የሥራ ቦታ (የቤት እና የህዝብ መኖሪያዎችን ያካትታል)፣ የቤት ወይም የሥራ ጂኦግራፊያዊ አቅጣጫ
19. በቤተሰብ ውስጥ የጥቃት ሰለባ መሆን (ቤትን ያጠቃልላል)፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ የፆታ ጥቃት እና መከታተል ሰለባ የሆነ ሰው

እባክዎ እነኝህ ትርጉሞች ሁሉን ያላከተቱ መሆናቸውን ይገንዘቡ።

441 4th Street NW, Suite 570N
Washington, DC, 20010
(202) 727-4559

ohr.dc.gov
facebook.com/dcohr
twitter.com/dchumanrights